DC public library

አካባቢዎን ይወቁ

የዲሲ የህዝብ ቤተ መፃህፍት የስትራቴጂክ ዕቅድ 2017–2021

# ዋና ማጠቃለያ



የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት (District of Columbia Public Library) (DCPL) ዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ ተጠቃሚዎች ከተለያየ የዘር ዓይነት መሆናቸውን የሚያንጸባርቅ የተወደደ ተቋም ነው— አዲስ የመጡ እንዲሁም የረጅም ጊዜ ነዋሪዎች እና ከአንድ ወገን፣ ዘር፣ የታሪክ መሠረት ያላቸው ነዋሪዎች። ሆኖም ዲ.ሲ ታላቅ እድገት እና ባላት የተለያየ የዘር ዓይነት ባለጸጋ ብትሆንም በርካታ ነዋሪዎች አስተማማኝ ሥራ ለማግኘት፣ ለሥራው ዓለም ብቁ የሚያደርግ ትምህርት ለመማር፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ ወይም መሰረታዊ መረጃ እና የኮምፒውተር ክህሎት ለማዳበር ተፈታታኝ ሁኔታዎች መጋፈጣቸውን ቀጥለዋል።

ሁሉም ነዋሪዎች በማገልገል እንደ አንድ ወሳኝ የማህበረሰብ ተቋም ሆኖ ያለውን መልካም ስም ለማጠናከር ቤተ መጻሕፍቱ ለእያንዳንዱ ሠፈር አዳዲስ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ እንዲሁም በተሻለ ለማገልገል የሚያቀርበውን አገልግሎት ለማሻሻል ቁርጠኛ ነው— በተለይ በጣም እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች በሚረዱ መንገዶች። ይህ የስትራቴጂክ ዕቅድ፤ ለእነኚህ ተፈታታኝ ሁኔታዎች የራሱን ምላሽ ለመስጠት፤ ቤተ መጻሕፍቱ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ለሚኖሩት ሥራዎች ዋና የመመሪያ ንድፍ ሆኖ ያገለግላል። ዕቅዱ መመስረቱን ለማሳወቅ እና በሂደቱ ውስጥ የእያንዳንዱ ሰው ድምጽ መሰማቱን ለማረጋገጥ፤ ቤተ መጻሕፍቱ በ2015 መጨረሻ ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ ነዋሪችን የዳሰሰ የተጠናከረ ከተማ-አቀፍ የማህበረሰብ ፍላጎት ግምገማ አካሂዷል። ጠቃሚ የአስተያየት ምላሽ የቀረበው ከ2,000 በላይ በሆኑ ነዎሪዎች እና 200 የቤተ መጻሕፍት ሠራተኞች በስልክ በተደረጉ ጥናቶች፣ የማህበረሰብ ስብሰባዎች፣ የአማካሪ ቡድኖች እና የድረ-ገጽ ጥናቶችን ጨምሮ በተለያየ መንገድ ቤተ መጻሕፍቱ፡-

- በመላው ዲ.ሲ ከሚገኙ ነዋሪዎች በስልክ ወይም በኦንላይን የዳሰሳ ጥናት የአስተያየት ምላሽ ሰብስቧል፤
- በመላ ዲስትሪክቱ ውስጥ በሚገኙ ቅርንጫፎች በተደረጉ የማህበረሰብ ውይይቶች ሕዝቡ እንዲሳተፍ አድርጓል፤
- የዲሲ ዜጎችን ለሚወክሉ የማህበረሰብ አጋሮች እና አገልግሎት አቅራቢዎች ተከታታይ የአማካሪ ቡድኖችን አስተናግዷል፤ እንዲሁም
- ለቤተ መጻሕፍት ሠራተኞች የዳሰሳ ጥናት እና የአማካሪ ቡድኖችን አደራጅቷል

### ከ 2,000 በላይ የሆኑ ነዋሪዎች እና 200 የቤተ መጻሕፍት ሰራተኞች ለስትራቴጂያዊ ዕቅድ ጠቃሚ የአስተያየት ምላሽ ሰጥተዋል

| የአስተያየት ምላሽ ዘዴ | ተሳታፊዎች |
|---|---|
| በስልክ የዳሰሳ ጥናት | 600 |
| የድረ-ገጽ የዳሰሳ ጥናት | 1,526 |
| የማህበረሰብ ስብሰባዎች፡- በTenley-Friendship፣ Shaw እና Anacostia ቤተ | 50 |
| የሠራተኞች የአማካሪ | 74 |
| ቡድን | 150 |
| የሠራተኞች | 72 |

**ቤተ መፃህፍቱ ለህብረተሰቡ የሚያበረክተው ዋጋ ተሳትፎ መሆኑን በመረዳት፤ የሚከተለው ንድፍ በ 2022 ተግባራዊ ከሆነ ስኬታማ እንደሆነ ይገነዘባል፡-**

75% የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች ንቁ የዲሲ የህዝብ ቤተ መፃህፍቶች ተሳትፎ ሲኖራቸው።

5 ሚሊዮን የቤተ መፃህፍት ንብረቶች በየዓመቱ በብድር ሲወጡ።

5 ሚሊዮን ወደ ቤተ መፃህፍት የሚደረጉ ጉብኝቶዎች እና በሚደረጉ ዝግጅቶች ላይ የሚኖረው ተሳትፎ በዓመት አምስት ሚሊዮን ሲሆን።

*ያ ራዕይ የተቀረፀው በአንዲት ቀላል መርህ ነው፡- ሰፈርህን እወቅ።*

በዲስትሪክቱ ዙሪያ ነዋሪዎች፤ የወደፊቱ ቤተ መጻሕፍት እንደ አንድ የማህበረሰብ መማሪያ ማዕከል ከሰፈር ቅርንጫፎች ጋር በመሆን ማህበረሰባቸውን በልዩ ሁኔታ የሚያገለግል ሆኖ እንደሚታያቸው ተናግረዋል። በተጨማሪም ቤተ መጽሕፍቱ፤ ጥራት ያላቸው መጻሕፍትን እና ሌሎች የተለመዱ እገዛዎች ለአካባቢው ነዋሪዎች ዋነኛው ፍላጎት ሆኖ አግኝተውታል፤ እንዲሁም አብዛኛዎቹ ነዋሪዎች አሁንም ድረስ ያሉትን የቤተ-መጻሕፍትን ፕሮግራሞች እና አዳዲስ አገልግሎቶችን አያውቁም።

ለዚህ ሰፊ የማህበረሰብ ተደራሽነት ምስጋና ይግባውና፤ ለቤተ-መጻህፍቱ ያለው የቀጣይ አምስት ዓመታት ራዕይ ግልጽ ሆኗል። ያ ራዕይ የተቀረፀው በአንዲት ቀላል መርህ ነው፡- ሰፈርህን እወቅ፤ ይህም ማለት እያንዳንዳቸው ቤተ መፃህፍት የሚያገለግሉትን ልዩ ማኅበረሰብ የሚንጸባረቅ አገልግሎት ማመቻቸት አለባቸው። ይህም በሁሉም ነዋሪዎች መካከል በተለይ አገልግሎቶችን እና መገልገያዎችን ለማግኘት ፈጽሞ ዕድል ለሌላቸው ወይም የማግኘት ዕድላቸው ውሱን ለሆኑ ሰዎች ፍትህን የማራመድ ትኩረት መስጠትን ያጠቃልላል።

DCPL በስትራቴጂክ ዕቅዱ አማካኝነት የዲስትሪክቱን ነዋሪዎች ኑሮ እና ደህንነታቸውን ለማሻሻል የሚከተሉትን አራት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ማሻሻያዎች ለማድረግ ቃል ገብቷል 1) ንባብ 2) የዲጂታል ዜግነት 3) ጠንካራ ማህበረሰቦች እና 4) የአካባቢ ታሪክ እና ባህል። እቅዱን በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል፤ ቤተ መፃህፍቱ በማህበረሰብ ፍላጎቶች ዙሪያ የሚኖሩትን የመገልገያዎች አቅርቦት እና ምላሽ ሰጪነትን ለማረጋገጥ በአስተባባሪነት ላይ ያተኩራል።

ቤተ መፃህፍቱ ከታች የተነደፈው የአምስት-ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ ላይ ለመድረስ ሶስት አስፈላጊ አመልካቾችን አዘጋጅቷል። ቤተ መፃህፍቱ ለህብረተሰቡ የሚያበረክተው ዋጋ ተሳትፎ መሆኑን በመረዳት፤ የሚከተለው ንድፍ በ 2022 ተግባራዊ ከሆነ ስኬታማ እንደሆነ ይገነዘባል፡-

- 75 ከመቶ የሚሆኑት የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች ንቁ የዲሲ የህዝብ ቤተ መፃህፍቶች ተሳትፎ ሲኖራቸው፤
- አምስት ሚልዮን የቤተ መፃህፍት ንብረቶች በየዓመቱ በብድር ሲወጡ፤ እና
- ወደ ቤተ መፃህፍት የሚደረጉ ጉብኝቶዎች እና በሚደረጉ ዝግጅቶች ላይ የሚኖረው ተሳትፎ በዓመት አምስት ሚሊዮን ሲሆን።

እያንዳንዱ ቅድሚያ የሚሰጠው አካባቢ እና ተዛማጅ ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑትን የቤተ-መጻህፍት መርሃ ግብሮች እና አገልግሎቶች ያንፀባርቃሉ።

**ንባብ፡-**አዲስ አንባቢዎችን መደገፍ እና የማንበብ ፍቅር እንዲኖራቸው ማበረታታት።

**ቤተ መፃህፍቱ ማንበብ እና መፃፍ የሚገነቡ እና የሚያበረታቱ አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞችን ያቀርባል።**

ዲስትሪክቱ በአገሪቱ ውስጥ እጅግ አንባቢ ናቸው ከሚባሉ ከተሞች አንዱ እንደሆነ በሰፊው ይታመናል፤ እናም ተጠቃሚዎች ከተለመዱ መፃህፍት እና መጽሄቶች እስከ ኢ-መፃህፍት እና የኦዲዮመጽሓፍቶችን የመሳሰሉ የቤተመጻሕፍት መገልገያዎችን በንቃት መጠቀማቸው ይህን የማንበብ ጥልቅ ፍቅር ያንጸባርቃል።

ሆኖም ግን ለሁሉም ትጉ አንባቢዎቹ፤ ዲስትሪክቱ በአዋቂዎችም ሆነ በልጆች መሃል በመላ ሃገሪቱ ከሚገኙ ሌሎች ከተማዎች ውስጥ እንደሚታየው የትምህርት እና የውጤት ከፍተኛ ክፍተት የማይታይበት አይደለም። በዚህ ምክንያት ቅድሚያ የሚሰጠው ዋንኛ ጉዳይ በአዲስ እና በተስፋፉ የቤተ መጻሕፍት ፕሮግራም እና አገልግሎቶች በማንበብ፣ በመጻፍ እርዳታ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆኑ ነዋሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ ማገናኘት ይሆናል። በርካታ ነዋሪዎች ማንበብ እና መጻፍ ሲጀምሩ ከተማው በሙሉ ይሻሻላል።

አዳዲስ አንባቢዎችን ለመደገፍ እና የማንበብ ፍቅርን ለማዳበር፤ ቤተ መፃህፍቱ፡-

- የንባብ ባህልን እና የማንበብ ታላላቅ ጥቅሞችን ያበረታታል። የህዝብ ቤተ መጽሐፍት አገልግሎቶችን ከተማሪዎች እና ከአስተማሪዎች ጋር ያገናኛል።
- አንባቢዎችን ለሚያዘጋጁ አዋቂዎች አገልግሎቶችን ያስፋፋል።
- የቤተ መፃህፍትን መፃህፍት እና ሌሎች ቁሳቁሶችን አስተማማኝ እና ምቹ የሆነ የማግኛ መንገድ መኖሩን ያረጋግጣል።

## **ዲጂታል ዜግነት፡-** ነዋሪዎችን ለኦንላይን ህይወት ማዘጋጀት

### ቴክኖሎጂ፤ የኢንተርኔት አገልግሎት እና ስልጠና በመስጠት ዲጂታል ዜግነትን መደገፍ

የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች የቴክኖሎጂ እና የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲሁም የዲጂታል ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ ዕድሎችን ለማግኘት ወደ ቤተ-መጻሕፍት ይሄዳሉ። የቤተ-መጻህፍት ዲጂታላዊ አገልግሎት ለአዛውንቶች፣ ለአፍሪካ-አሜሪካዊያን እና ለላቲኖ ነዋሪዎች ይበልጥ አስፈላጊ ነው።

ከዚህም ባሻገር የኢንተርኔት አገልግሎት መደበኛ እና በማያቋርጥ ሁኔታ ለበርካታ ሰዎች መድረሱ እየቀጠለ ሳለ፤ ከመድረሱ ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙት ውስብስብ ነገሮች ነዋሪዎች ለኦንላይን ህይወት ዝግጁ እንደሆኑ ለማረጋገጥ ከቤተ-መጻህፍት ከፍተኛ ጥረት ይጠበቃል። ነዋሪዎቹ የበለጠ ጊዜያቸውን በኦንላይን ላይ ሲያጠፉ የኦንላይን ላይ ደህንነት፣ ዲጂታል ስነ-ምግባር እና ተዛማጅ የዲጂታል እውቀት አስፈላጊነትን መገንዘብ ወሳኝ ነው።

የዲስትሪክቱን የተጎዱ ህዝቦችን ለማገልገል እና ለስራ እና ለህይወት ስኬታማነት ለማዘጋጀት፤ ቤተ መፃህፍቱ፡-

- ነዋሪዎች እየጨመረ የመጣውን የዲጂታል ዓለም ለመምራት ችሎታ እንዳላቸው ያረጋግጣል።
- በጣም በሚፈልጉት ማህበረሰብ ውስጥ የቴክኖሎጂ እና የኢንተርኔት አገልግሎት ያስፋፋል።



**ጠንካራ ማህበረሰቦች**-የአካባቢ ቤተ-መጻህፍት የህብረተሰብ መማሪያ እና የህዝብ መሳተፊያ ማዕከል ናቸው።

**በአገልግሎቶች፣ በፕሮግራሞች፣ ዘልቆ በመድረሻ አገልግሎት አማካኝነት ማህበረሰቦችን ማጠናከር እና በቤተ መፃህፍት አካባቢያዊ ካምፓስ መጠቀምን መጨመር።**

የቤተመፃህፍት ቅርንጫፎች ሁልጊዜ በሚያገለግሏቸው ማህበረሰቦች ማዕከላዊ ቦታዎች ላይ ናቸው። የረጅም ጊዜ ነዋሪዎች የመሰብሰቢያ ቦታ እና የአዲስ መጤዎች እርስ በርስ ለመተባበር እና እርስ በእርስ ለመማር የሚያገለግላቸው የሰፈራቸው ተጨማሪ ክንፍ ናቸው። በማህበረሰብ ተሳትፎ ሂደት በኩል ነዋሪዎች ቤተ-መፃህፍት በማበረሰቡ ውስጥ ያለውን ሚና እንዲያስፋፉ ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል። በተጨማሪም ዘልቆ የመድረሻ አገልግሎት DCPL ን በአገልግሎቱ ይበልጥ የሚደገፉ እና ተጠቃሚ የሚሆኑትን ነዋሪዎችን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል እንደሚያስችለው አመልክተዋል።

ይህንን ዕድል ለመገንባት፤ ቤተ መፃህፍቱ:-

- ዝቅተኛ-ተጠቃሚዎች እና ፈጽሞ-ተጠቃሚ ያልሆኑትን አዲስ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ያደርጋል።
- የቤተ-መጻህፍትን አካባቢያዊ ካምፓስ መጠቀምን ይጨምራል።

**የአካባቢ ታሪክ እና ባህል**-ዲ.ሲ.ን ልዩ የሚያደርገውን ግንዛቤ እና አድናቆት ማዳበር

**የዲስትሪክቱን ነዋሪዎች ያሉትን ልምዶች እንዲያገኙ በማድረግ ከዲስቲሪክቱ የቀድሞ፣ የአሁን እና የወደፊት ታሪክ ጋር ማገናኘት እና ለአካባቢያዊ ታሪክ እና ባህል ድጋፍ መስጠት።**

ለዲስትሪክቱ ነዋሪዎች ከፍተኛ የኩራት ምንጭ የከተማው የደመቀ ባህል ነው - ያለው የቆየ የማህበረሰብ ታሪክ ከአዳዲስ አጎራባቾች እና ከመላው ዓለም የመጡ ስደተኞች ጋር ይጣጣማል። በፍላጎት ግምገማው መሰረት ነዋሪዎች በሚያገለግሉባቸው በየዓይነቱ ዘር ያቀፉ አካባቢዎች ውስጥ የቤተ መፃህፍት ቅርንጫፎችን እንደ ባህላዊ ማዕከሎች እንዲጠቀሙ ይፈልጋሉ።

የዲሲ ታሪክን እና በየጊዜው እያደገ የመጣውን ባህል ለማክበር፤ ቤተ መፃህፍቱ:-

- ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር በመተባበር የአካባቢ ታሪክ ስብስቦችን ያጠናክራል።
- ለነዋሪዎች የተለያዩ የአገር ውስጥ ታሪክ እና የባህል ፕሮግራሞችን ያቀርባል።.
- የፈጠራ ችሎታ ያለው የዲሲ ማህበረሰብ ለማደግ የሚያስፈልጉትን መገልገያዎች ለማግኘት በቤተመፅሐፍቱ ላይ መተማመን እንዲችል ያደርጋል።

**ዕቅዱን ከግብ ማድረስ— በንቃት መጠበቅ፦** ቤተ መፃህፍቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለሚለዋወጡት የማህበረሰብ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት በተጠንቀቅ መቆሙን ማረጋገጥ።

አራቱን ቀዳሚ ግቦችን ለማከናወን፤ ቤተ መፃህፍቱ ለሚነሱ አዳዲስ ሃሳቦች ምላሽ በመስጠት የከተማውን ስነ-ሕዝብ እና አዲስ ቴክኖሎጂዎችን መለወጥ እንዲችል የራሱን ውስጣዊ አሰራር ላይ ማተኮር ይኖርበታል። የመገልገያ ሀብቶች ጥሩ ጠባቂ በመሆን- ለቤተ-መጻሀፍት አዳዲስ የመገልገያ ሀብቶችን መገንባት እና ያሉትን ነባር የመገልገያ ሀብቶችን በመመደብ እና በማጠናከር - ቤተ መፃህፍቱ የዲስትሪክቱን ነዋሪዎች በተሻለ ሁኔታ ያገለግላል።

የስትራቴጂክ ዕቅዱን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ፤ ቤተ መፃህፍቱ፦

ከሁሉም በላይ ቤተ መፃህፍቱ የሚያገለግላቸው የማህበረሰቡ አባላት ከሚያደርጉለት እገዛ ጋር ይህ የጋራ ራዕይ እውን ይሆናል፣ እንዲሁም ዝግጁ እና ባለጸጋ ለሆኑ ነዋሪዎች አስተዋፅኦ ያበረክታል።

- የቤተ-መጻሕፍት መገልገያ ሃብቶችን ከማህበረሰብ ፍላጎቶች ጋር ያመጣጥናል።
- ማህበረሰቡን በተሻለ መንገድ ለማገልገል የቤተ-መጻህፍት ቦታዎችን ያቅዳል እንዲሁም ዲዛይን ይነድፋል። ሁሉንም የቤተ-መጽሐፍት አገልግሎቶች ገጽታዎች ለማሻሻል መረጃ ይጠቀማል።
- ቤተ-መጻህፍቱ ያለውን አውንታዊ ተጽእኖን ለማጠናከር ከውጪ የገንዘብ እና የመገልገያ ሀብቶች እርዳታ ያፈላልጋል።
- ለሚኖረውን ለውጥ ያለወን እውቀት እና ግንዛቤ ይጨምራል

እነዚህ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቦታዎች በስትራቴጂክ ዕቅድ ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል። አንድ ላይ በመሆን ቤተ-መጻህፍቱን ወደ እድገት እና ስኬት የሚያመራ ጠንካራ የሆነ ተግባራዊ ፕላን ይፈጥራሉ።

የታለመውን የአምስት ዓመት ዕቅዱ ለማሳካት እነዚህን ጥረቶች የሚደግፉ ወይም ከእነዚህ ጥረቶች ጥቅም ከሚያገኙት ሁሉ ተሳትፎአቸውን ይጠይቃል። እንዲሁም ቤተ መፃህፍቱ በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ከሁሉም ነዋሪዎች የሚሰጠውን አስተዋፅኦ ይቀበላል። ከማህበረሰቡ አጋሮች፣ የቤተ መፃህፍት መሪዎች እና ሰራተኞች፣ እንዲሁም ከሁሉም በላይ ቤተ መፃህፍቱ የሚያገለግላቸው የማህበረሰቡ አባላት ከሚያደርጉለት እገዛ ጋር ይህ የጋራ ራዕይ እውን ይሆናል፣ እንዲሁም ዝግጁ እና ባለጸጋ ለሆኑ ነዋሪዎች አስተዋፅኦ ያበረክታል።